THE BRIDGEFUND

DMPED OFFICE OF THE DEPUTY MAYOR FOR PLANNING & ECONOMIC DEVELOPMENT

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# RETAIL BRIDGE FUND

## በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ማውጫ


**ብቁነት** .......... Error! Bookmark not defined.

**የማመልከቻ ሂደት** .......... 2

**የድጋፍ ገንዘብ** .......... Error! Bookmark not defined.


## ብቁነት

**ሱቄን ለጊዜው ዘግቻለሁ። አሁንም ብቁ ነኝ?**
አይደሉም። ለጊዜው የተዘጉ የንግድ ቦታዎች (ከታች እንደተገለፀው) ብቁ አይደሉም። ነገር ግን በተወሰነ አቅም የሚሰሩ የንግድ ደርጅቶች (ከታች እንደተገለፀው) ብቁ ናቸው።

- ለጊዜው የተዘጉ = የንግድ ቦታው ለህዝብ የተዘጋ እና ምርቶችን በድህረ ገፅ ላይ ከሱቅ መቶ ለመውሰድ ወይም እቃውን ለማድረስ የማይሸጥ ከሆነ ነው።
- የተወሰነ አቅም = የተወሰነ አቅም የሚከተሉት ምድቦች ውስጥ ይወድቃል (1) የንግድ ቦታው ለህዝብ የተዘጋ ሆኖ ምርቶቻቸውን በድህረ ገፅ ላይ ከሱቅ መተው ለመውሰድ ወይም እቃውን ለማድረስ የሚሸጡ ሲሆን ነው። ወይም (2) የንግድ ቦታው ተከፍቶ ሰአት ቀንሰው የሚሰሩ ከሆነ ነው።

**ንግዴን በቋሚነት ዘግቻለሁ። በፊት የነበሩኝን ኪሳራዎች ለማካካስ ማመልከት እችላለሁ?**
አይቻልም። ይህ የድጋፍ እድል አሁን ክፍት የሆኑ የንግዶችን ለበደገፍ የተዘጋጀ ነው።

**መደብር የለኝም ፣ ግን ምርቶቼን በጋራ የመሸጫ ሱቅ ውስጥ እና/ ወይም ገበያዎች እና ጊዜያዊ የመሸጫ ስፍራዎች እና ዝግጅቶች ላይ ነው የምሸጠው። ብቁ ነኝ ወይ ?**
አይደሉም። የዚህ የድልድይ ድጋፍ ገንዘብ አላማ ትልልቅ ቋሚ ወጪዎች ያላቸውን መደብሮች ለመደገፍ ነው። የነዚህ ፊት ለፊት ያሉ መደብሮች ክፍት ሆኖ መቆየት ለኮሪደር ህያውነት አስፈላጊ ናቸው። እናም አምራቾች ምርቶቻቸውን የሚሸጡበት ቦታ እንዲኖራቸው ይጠቅማል።

**ለተለያዩ የድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት እችላለሁ ወይ? ለምሳሌ ሬስቶራንቴ ውስጥ ትንሽ እቃ መሸጫ መደብር ቢኖረኝ ፣ ለሁለቱም ለሬስቶራንት እና ለመደብር የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት እችላለሁ?**
አይችሉም። እያንዳንዱ የቢዝነስ ቦታዎች አንድ የድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ነው ማግኘት የሚችሉት። የትኛ ድጋፍ ለእርሶ ንግድ እና ዋና የገቢ ምንጭ የበለጠ እንደሚስማማ ለመወሰን፤ የድጋፉን ማመልከቻ መመሪያ እና የብቁነት ሰንጠረዡን በጥንቃቄ እንዲያነቡት እናበረታታለን።

**የምግብ አገልግሎት ለመስጠት ነው የተቋቋምኩት። ለመደብር ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት አለብኝ?**
ሁሉም የምግብ እና የመጠጥ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋሙ ንግዶች ለዚህ ፕሮግራም ብቁ አይደሉም። እነዚህ ንግዶች ለሬስቶራን ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የአካል ብቃት መስጫ ነው ያለኝ። ለመደብር ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት አለብኝ?**
ጂም፣ የአካል ብቃት፣የዳንስ እና የዮጋ ስቱዲዮዎች ለዚህ ፕሮግራም ብቁ ናቸው።

**ከአንድ በላይ ንግድ አለኝ። ከአንድ ጊዜ በላይ ለመደብር ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት እችላለሁ?**
ይችላሉ። የተለያየ ኢአይኤን ላላቸው እያንዳነዱ ንግዶች ማመልከት ይችላሉ። ነገር ግን፣ ከፍተኛ ማስገባት የሚችሉት ማመልከቻዎች 5 ለአንድ ባለቤት ነው።

**ንግዴን የከፈትኩት የወረርሽኙ ቀደም ብዬ ነው (በማርች 17)፣ ግን ከአንድ አመት በላይ አልተከፈተም። ንግዴ ለድጋፉ ብቁ ነው?**
አዎ። ግን ፋይናንሱ ላይ በወረርሽኙ ምክኛት 25% እና ከዚያ በላይ የኢኮኖሚ ጉዳት እንደደረሰብዎት ሊያሳዩ ይገባል።

**የኤስ ቢ ኤ የአደጋ ብድር ቀደም ብሎ በዚህ አመት አግኝቻለሁ። ለሱቅ ድጋፍ ብቁ ነኝ ?**
አዎ፣ የኤስ ቢ ኤ ገንዘብ የድጋፉ ብቁነቶ ላይ ተፅዓኖ የለውም።

**ከሌላ የዲሲ መንግስት ኤጀንሲ የገንዘብ ድጋፍ አግኝቻለሁ። ለሱቅ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ነኝ ?**
ለማመልከት ብቁ ኖት ግን ሌላ ድጋፎች ሊያገኙ የሚችሉትን የገንዘብ መጠን ላይ ተፅዓኖ ሊኖራቸው ይችላል።

**ፍራንቻይዞች ብቁ ናቸው ወይ ?**
አዎ፣ እራሱን ችሎ የሚተዳደር እና የሚሰራ ከሆነ ነው።

**ለትርፍ የማይሰሩ ሱቆች ለዚህ ድጋፍ ማመልከት ይችላሉ?**
ለትርፍ የሚሰሩ ንግዶች ብቻ ናቸው ብቁ የሆኑት።

**በራሳቸው የሚሰሩ ሰራተኞች ብቁ ናቸው? (ለምሳሌ ፡- ፀጉር ሰራተኞች ፣ የኮስሞቶሎጂ ባለሙያ፣ ማሳጅ ቴራፒስት፣ የአካል ብቃት አሰልጣኝ)**
አይደሉም፣ መደብር ሊኖሮት ይገባል ( ለምሳሌ፡- የፀጉር ቤት፣ ማሳጅ አገልግሎት መስጫ ቦታ፣ የአካል ብቃት ስቱዲዮ፣ ወዘተ.)።

**ሶል ፕሮፕራይተሮች ለሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ናቸው?**
ድጋፉን ለማግኘት ብቁ የሚሆኑት መደብራቸው በዲሲ ሲገኝ እና የዲሲ ነዎሪ ሲሆኑ ነው።

**ሱቅ ያለው የሀይማኖት ተቋም ነኝ ። ማመልከት እችላለሁ ?**
ለብቻው የሆነ ለትርፍ የተቋቋመ የሱቅ ንግድ ካልዎት፣ ለንግዱ ማመልከት ይችላሉ። የሀይማኖት ተቋማቶች በራሳቸው ለ ሱቅ ድልድይ የገንዘብድጋፍ ብቁ አይደሉም።

**የአልኮል አምራች፣ ወይን ጠማቂ፣ ቢራ ጨማቂ ወይም ኮምጣጤ አምራች ነኝ። ለሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ ነኝ ?**
ለሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ የሚሆኑት የአምራቾች ፍቃድ A ወይም B ከያዙ ወይም ከማምረቻው ቦታ ውጪ የሱቅ ፈቃድ ከአብራ ያገኙ ከሆነ ነው።አመልካቾች በቦታው ላይ የሱቅ ፈቃድ ከያዙ (እንደ ታቨርን ወይም የምሽት ከበብ ፈቃድ )፣ ለሬስቶራንት ወይም ለመዝናኛ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ነው ማመልከት ያለባቸው። የታቨርን ፍቃድ እና የምግብ ሽያጭ 25 % እና ከዚያ በላይ የገቢዎ ምንጭ ከሆነ ለሬስቶራንት ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ያመልከቱ። የምሽት ከበብ ፈቃድ ወይም የታቨርን ፈቃድ ኖሮት ግን ከምግብ የሚያገኙት ሽያጭ ከ 25% የገቢ ምንጭ የሚያንስ ከሆነ ለመዝናኛ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ያመልከቱ።

**የአካባቢ ንግድ ኢንተርፕራይዝ ((LBE) ብቁ የሆኑ ንግዶች ምን ማለት ነው ?**
LBE ማለት በንግድ ኢንተርፕራይዝ የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ምድብ ውስጥ ሲሆን፣ በትንንሽ እና አካባቢያዊ ንግዶች እድገት (DSLBD) ክፍል የሚተዳደር ነው። የ LBE ትርጉም ከታች እንደተፃፈው

- ዎናው ቢሮ ዲሲ ውስጥ ሲገኝ ነው፤
- ዋና ስራ አስኪያያጅ እና ከፍተኛ ደረጃ አስተዳዳሪ ሰራትኞች ቢሯቸውን እና የአስተዳደር ስራቸውን በዲስትሪክት ውስጥ ሲያደርጉ ነው፤
- ከነዚህ አራት ነረሮች አንዱን ሲያሟሉ ነው፡
    - ከ 50% በላይ ንብረት ባንክ አካውንትን ሳይጨምር በዲስትሪክት ውስጥ ሲሆን ነው፤
    - ከ 50% በላይ ሰራተኞች በዲስትሪክት ነዋሪ ሲሆኑ ነው፤
    - ከ50% በላይ የሚሆነው የንግዱ ኢንተርፕራይዙ ባለቤቶች የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው፤
    - ከ 50% በላይ የሚሆነው አጠቃላይ ሽያጭ ወይም ሌላ ገቢዎች ከዲስትሪክት ግብይት የመጣ መሆን አለበት።More t
- በዲሲ ህግ መሠረት በትክክል ፍቃድ ያለው ነው፤ እና
- በዲቺ ህግ መሠረት ታክስ ከፋይ ከሆኑ ነው (ምዕራፍ18 ርዕስ 47)

**ብቁ ያልሆኑ የንግድ አይነቶች አሉ ?**

የሚከተሉት ንግዶች ለ ሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ አይደሉም ፡

- ኢ ኮሜርስ ንግዶች
- የቤት ውስጥ ንግዶች
- ወቅታዊ ንግዶች (በአመት ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚከፈቱ)
- የጤና እንክብካቤ እና የማህበረሰብ እርዳታ (ዶክተሮች, የጥርስ ህክምና ባለሙያዎች፣ አኩፓንቸር፣ እና ኪሮፕራክተር ቢሮ ወዘተ.)
- የልጅ እንክብካቤ ሰጪዎች
- ፋይናንሻል ተቋማት (ባንክ፣ ክሬዲት ዩኒየን፣ ቼክ የሚመነዝሩ ተቋማት፣ ለመክፈል የሚያበድሩ ወዘተ.)
- ሙያዊ አገልግሎቶች (የሒሳብ ባለሙያ፣ ኢንሹራንስ፣ የጠበቃ ቢሮ ወዘተ.)

- ግንባታ እና ሪል እስቴት (አጠቃላይ ግንባታ፣ አርክቴክቸር፣  ግንባታ፣ ንብረት ማስተዳደር፣ የቤት ደላላ ወዘተ)
- በግል የሚሰሩ  (ማሳጅ ቴርፒስት፣ የፀጉር ባለሙያ፣ የኮስሞቲሎጂ ባለሙያ፣ የጥፍር ሰራተኛ፣ የአካል ብቃት አሰልጣኝ፣ የዳንስ አስተማሪዎች ወዘተ.) የራሳቸው የሱቅ ቦታ የሌላቸው
- ምርቶቻቸውን በጋራ የመሸጫ ቦታ የሚሸጡ ግን መደብሩን ያልተከራዩ ወይም የራሳቸው ያልሆነ

# የማመልከቻ ሂደት

**የበዕል ወቅት ለባለሱቆች ስራ የሚበዛበት ወቅት ነው። ማመልከቻዬን ወዲያው ማመልከት እንደተጀመረ ካላመለከትኩ፣ ልቀጣ እችላለሁ?**
ይህ ድጋፍ መጀመሪያ የመጣ መጀመሪያ የሚያገኝበት አይደለም። ማመልከቻውን የምናየው እንደመጣ ነው፣ ግን ተሸላሚዎችን የምናጠናቅቀው ከማመልከቻው መዝጊያ በኋላ ነው።

**ለማይክሮግራንት ፕሮግራም የተጠቀምኩትን የንፁህ እጅ ምስክር ወረቀት ማስገባት እችላለሁ?**

አይቻልም። በምታመለክቱበት ጊዜ አዲስ የንፁህ እጅ ምስክር ወረቀት ከማመልከታችሁ በፊት በ90 ቀን ውስጥ ሊሆን ይገባል።

**መሰረታዊ የንግድ ፈቃድ የለኝም። ለሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከት እችላለሁ ?**
አይችሉም። የሚሰራ የዲሲ የንግድ ፈቃድ ኮፒ ከገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻችሁ ጋር  አብራችሁ ማስገባት አለባችሁ።

**ሰነዶቹን በሰአት ማስገባት ካልቻልኩስ ?**
ብቁ ለመሆን ፣ የንግድ ድርጅቶቹ ሁሉንም የተጠየቁ ሰነዶች ከማመልከቻችሁ ጋር ማስገባት ይኖርባችኋል።

**ማመልከቻዬን በኢ ሜይል ማስገባት እችላለሁ?**
አይችሉም። ሁሉም ማመልከቻዎች በተዘጋጀለት ድህረ ገፅ  ላይ ከ አርብ ጀንዎሪ 8 2020 5፡00 ሰዓት በፊት መግባት አለባቸው። ዲኤምፒኢዲ እና የፕሮግራሙ አጋሮች ለማይነበብ፣ ላላለቀ፣ እና/ ወይም በስነስርዓት ላልገባ ማመልከቻ ሀላፊነት አይወስዱም።

**ስለ ሰነዶቼ ማመልከቻዬን ከማስገባቴ በፊት መጠየቅ እችላለሁ?**

አዎ።በ RetailBridgeFund@dc.gov ላይ ጥያቄያችሁን በደንብ አብራርታችሁ ኢሜይል አድርጉ።

**ሰራተኞቼን ለጊዜው ከስራ ቀንሻቸዋለሁ ግን አላሰናበትኳቸውም። እነዚህን ሰራተኞች ማመልከቻዬ ላይ ማስገባት አለብኝ ?**
አይችሉም።የሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ በ ሴፕቴምበር 30 2020 ያለውን የሰራተኞቹን ቁጥር እና የደመወዝ ክፍያ ይጠይቃል። ለጊዜው ከስራ የተቀነሱ ሰራተኞች  ድምሩ ላይ መጨመር የለባቸውም እና/ ወይም በሴፕቴምበር 30 2020 ስራ ላይ ያሉ ሰራተኞች ነው የምታሳውቁት።

**በኮንትራት የሚሰሩ ሰራተኞችን በ ማመልከቻዬ ላይ እንደ ሰራተኞቼ ማስገባት እችላለሁ ?**
አዎ። የሰራተኞችን ቁጥር ሲያስገቡ ኮንትራክተሮችንም መጨመር ትችላላችሁ። ሙሉ ሰዓት ሰራተኞችዎን፣ ከፊል ሰዓት ሰራተኞችዎን እና ኮንትራት ሰራተኞችዎን ለያይተው በደሞዝ መክፈያ ሰነዳችሁ ላይ አስቀምጡ።

# የድጋፍ ገንዘብ

**ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የማገኘው የገንዘብ ድጋፍ ስንት ነው?**

ዝቅተኛው ድጋፍ $5000 እና ከፍተኛው ድጋፍ ደግሞ25000 ነው።

ስንት እንደማገኝ እንዴት ነው የሚወሰነው?
የድጋፉ መጠን የሚወሰነው የዲሲ ነዋሪ ሰራተኞች ቁጥር፣ የንግድ ቆይታ፣ እና ቋሚ ወጪዎችን መሰረት አድርጎ ነው።

**መቀበላቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ መቼ ነው የሚደርሰኝ?**

እንደተቀበልናችሁ የሚያሳውቅ ደብዳቤ ከጀንዋሪ መጨረሻ ላይ ይደርሳችኋል ብለን እናስባለን።

**ለሱቅ ድልድይ የገንዘብ ድጋፍ አመልክቻለሁ። ድጋፉን እንደማገኝ እርግጠኛ ነው ?**
አይደለም። ይህ ተወዳዳሪ የምርጫ ሂደት ስላለው ለድጋፍ ስላመለከታችሁ ድጋፍ ታገኛላችሁ ማለት አይደለ። ተሸላሚዎች የሚመረጡት የንግዱን ህያውነት፣ የሰራተኞች ቁጥር እና የቆየበት ጊዜ መሰረት አድርጎ ነው።

**የድጋፍ ገንዘቡን በ2020 መጀመሪያ ላይ የነበሩኝን ወጪዎችን  ለመሸፍን መጠቀም እችላለሁ?**
የድጋፍ ገንዘቡን መጠቀም የሚቻለው ከ ድጋፍ ስምምነቱ በኋላ የሚመጡ ወጪዎችን ለመሸፈን ነው።

**ለምን ያህል ጊዜ ነው የድጋፍ ገንዘቡን ማጥፋት የምችለው ?**
የድጋፍ ገንዘቡ ከ ጁን 30 2021 ድረስ ማውጣት አለባችሁ።

**የድጋፍ ገንዘቡን ከተቀበልኩ በኋላ ምን ይሆናል ?**
ገንዘቡን የተፈቀዱ ወጪዎች ላይ ካጠፉን በኋላ፣ ንግዳችሁ እንዴት አድርጎ ብሩን እንደተጥቀመው ሪፖርት ትልካላችሁ።የድጋፍ ስምምነቱ ሪፖርት እንዴት እንደምታስገቡ መመሪያ ይሰጣችኋል።